# ለአገራችን ችግር መፍትሔ እናዋጣ

ኢትዮጵያ በዉድ ልጆቿ ቆራጥ ተጋድሎና መስዋዕትነት ነፃነቷን ጠብቃ የዘለቀች ታላቅ አገር የመሆኗን ያህል በየዘመናቱ የነበረዉ የፖሌቲካ አስተዳደር ሲታይ መንቀራቀስ የሞላበትና የየዘመኑ ፖሌቲከኞች ግኙኝነት በሽኩቻ የተሞላ መሆኑ አሳዛኝም አሳፋሪም ታሪክ እንደሆነ ቀጥሏል፡፡ ይኼዉ ለዘመናት የዘለቀዉ ችግራችን አሁን በደረስንበት ደረጃም መልኩን ቀይሮ ወንድሙን በሚገድል ቃየላዊ መንፈስ ተሞልቶ እንደአገር የመቀጠላችን ጉዳይ ለመተንበይ በሚያዳግት ዘመን ላይ አድርሶናል፡፡ የነፃነት ታሪካችን ተገቢዉን የታሪክ ከፍታ ይዞ መቀጠል የሚችለዉ ኢትዮጵያ የምትባል አገር እንደ አገር መቀጠል እስከቻለች ድረስ ብቻ ነዉ፡፡ ይሁንና የዘመናችን ፖሌቲከኞች ይህችን አገር ክብር በሚመጥን የፖሌቲካ ደረጃ ላይ ስለመሆናቸዉ እስኪንጠራጠር አገር እየፈረሰ መደማመጥና መቀባበል አቅቷቸዉ አገሪቱ ስለተያያዘችዉ የዉድቀት ጉዞ አንዱ ሌላዉን ከመወንጀል ያለፈ መፍትሔ አመንጪዎች አልሆኑም፡፡ በዘመናችን በአሳዛኝ ሁኔታ አገራችን የጋራ ቤታችን መሆኗ ቀርቶ የራስን አንጃ በመመስረት መቆራቆስና መለያየት ከመጠን በላይ አይሎና ጥላቻ ነግሶ ብሔር ተኮር ጥቃት እንደትግል ስልት ተወስዶ ንጹህ የሰዉ ደም እየፈሰሰ፤ ነፍስ እየጠፋ፤ በእንቅርት ላይ ጆሮ ገድፍ እንዲሉ ያለብን የከፋ ድህነት አልበቃ ብሎ የፈራ ሀብት በየቦታዉ በመዉደም ላይ መሆኑ ሲታይ ምን ያህል ማስተዋል እንዳቃተን ለመረዳት ተመራማሪ መሆን አያስፈልገንም፡፡ ታዲያ አገር በዚህ ደረጃ በከፋ ችግር ዉስጥ በወደቀችበት ወቅት የመልካም መካሪዎች መካን የመሆናችን ምስጢር ግራ የሚያጋባ ነዉ፡፡ ጠቢቡ ሰለሞን " የሰዉ መንገድ ሁሉ በዓይኑ ፊት የቀናች ትመስለዋለች" እንዳለዉ በየፊናችን የያዝነዉን የሙጥኝ ብለን ምኞታችንን ብቻ በመከተላችን የአገር ህልዉና አደጋ ላይ ወድቋል፡፡ ማናችንም ብንሆን ከምኞታችን በላይ የአገራችን ህልዉና ካላሳሰበን መድረሻችን ዉድቀት እንደሚሆን አሁንም የባነንን አይመስለኝም፡፡ ከዚህ በኋላ እስካሁን ላባከንነዉ ጊዜ በመፀፀትና ትምህርት በመዉሰድ አገራችንን ከዉድቀት አፋፍ የማትረፍ ጉዳይ የምርጫ ሳይሆን የግድ ብሎን ከምኞታችን ያለፈ የአርቆ አስተዋይነት ዉሳኔ ላይ መድረስ የግድ ይለናል፡፡ ከዚህ አንፃር የዘመኑ የአገራችን ፖሌቲከኞች የዚህችን ታላቅ አገርና ህዝብ ዕጣ-ፈንታ መወሰን በእጃቸዉ እንደወደቀ ተረድተዉ አገራችን ለተጋረጠባት አደጋ እርስበርስ መወነጃጀሉ ከመፍትሔነቱ ይልቁ የዉድቀቱን ጉዞ እንደሚያፋጥ አምነዉ ወደ መደማመጥና መቻቻል መንፈስ በመምጣት ህዝቡን ከአገርና መሪ አልባ ከማድረግ ሊታደጉት ይገባል፡፡ ስለሆነም ሁሉም እንደአቅሙ የመፍትሔ ሀሳብ በማመንጨት የመፍትሔ አካል ሊሆን ግድ ይላል፡፡ ከዚህ አንፃር በእኔ እይታ የታዩኝን የመፍትሔ ሃሳቦች እንደሚከተለዉ አቀርባለሁ፡፡

1. **የፖሌቲካ ምህዳርን በተመለከተ፡-** በአሁን ሰዓት አገሪቱን እየመራ ያለዉ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) ዘግይቶም ቢሆን አገሪቱ የገባችበትን ቀዉስ በመረዳት ጠ/ሚ/ሩ የስልጣን ጊዜያቸዉን ሳያጠናቅቁ የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ለፓርቲያቸዉና ለተወካዮች ም/ቤት አስገብተዋል፡፡ ይህ

ለአገራችን ፖሌቲካ በጎ ጅምር በመሆኑ ሁሉም የፖሌቲካ ኃይሎች ይህን ፈር ቀዳጅ ዉሳኔ አዎንታዊ ጎኑን በመወሰድ ለቀጣይ የፖሌቲካ ምህዳር መሻሻል እንደ ግብአት ለመጠቀም ዝግጁ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ጠቅላይ ሚ/ሩ የስልጣን መልቀቂያ ጥያቄ ማቅረባቸዉ አንድ ነገር ሆኖ በአሁን ሰዓት በአገሪቱ ላይ ያጎንበበዉን አደጋ ከግንዛቤ በመዉሰድ የሚኒስትሮች ም/ቤት ለ6 ወራት የሚቆይ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አዉጇል፡፡ በእኔ እምነት ሁሉም የፖሌቲካ ኃይሎች (ገዥዉም ሆነ ተቃዋሚ ፓርቲዎች) እዉነትም ለአገርና ለህዝብ ቅድሚያ ለመስጠት ተዘጋጅተዉ ከሆነ ይህን እንደመልካም አጋጣሚ በመዉሰድና ከዚህ በላይ የሚባክን ጊዜ እንደሌለ በመረዳት ያለዕንቅልፍ ሊሰሩ ይገባል፡፡ በዚህ ረገድ መዉሰድ ያለባቸዉ እርምጃዎች፡-

1.1. አሁን ባለዉ የአገሪቱ ህገመንግስት መሰረት ከ2 ዓመት በኋላ አገራዊ ምርጫ እስኪካሄድ ድረስ አገሪቱን የሚመራ አዲስ ጠቅላይ ሚ/ር በመሰየም አገሪቱ እየተመራች እንድትቀጥል የማድረጉን ጉዳይ የተቃዋሚዉ ጎራ ጭምር ባይስማማ እንኳን ባይቃወም ለአገሪቱ ህልዉና የተሻለ እንደሆነ ይሰማኛል፡፡

1.2. እስከ ቀጣይ አገራዊ ምርጫ ድረስ ባለዉ የ2 ዓመት ጊዜ ዉስጥ ሁሉም የፖሌቲካ ኃይሎች ተቀራርበዉ በመወያየትና በመደራደር ህገመንግስቱን ጭምር በማሻሻል ሁሉም የፖሌቲካ ኃይሎችና አብዛኛዉ ህዝብ የተቀበለዉ የህገመንግስት ሰነድ እንዲኖር ማስቻል ፋይዳዉ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ በዚህ ረገድ ቢያንስ ቢያንስ መግባባት (Consensus) ላይ የተደረሰበትና በሰጥቶ መቀበል መርህ የተዘጋጀ ህገመንግስታዊ ሰነድ አገራችን እንዲኖራት ማድረግ ከሁሉም በላይ ልናተኩርበት የሚገባና ሌላ የተሻለ አማራጭ የሌለዉ እንደሆነ መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

1.3. ከላይ በተራ ቁጥር 1.2. ላይ የተጠቀሰዉን ሂደት ለማስኬድ በመጀመሪያ ሁሉም የተቋዋሚ ኃይሎች (ነፍጥ ያነሱ ካሉም ጭምር) የሚሳተፉበት የድርድር መድረክ ሊዘጋጅ ይገባል፡፡ አደራዳሪዎችን በሚመለከትም ቢቻል ቢቻል የራሳችንን ችግር በራሳችን የመፍታት ልምድ እየዳበረ እንዲሄድም ጭምር ልምድ ያላቸዉ የአገራችን ምሁራን ከአንጋፋ ዩኒቨርስቲዎቻችንም ሆነ ከሌሎች ተቋማት ተሰይመዉ ድርድሩን የሚመሩበት ሁኔታ ቢፈጠር፤

1.4. በሚደረገዉ ድርድር ህገመንግስቱን በማሻሻል አብዛኛዉ ህዝብና የፖሌቲካ ኃይሎች የተቀበሉት የህገመንግስት ሰነድ እንዲኖረን መስማማት እስከተቻለ ድረስ የማሻሻል ሂደቱ የሚመለከታቸዉን ምሁራንን ያካተተና ስብጥሩ የሁሉም ፖሌቲካ ኃይሎች ይሁንታ ያለበት አባላትን የያዘ የህገመንግስት ማሻሻያ ኮሚሽን በጊዜያዊነት ተቋቁሞ የሚቀጥለዉ አገራዊ ምርጫ ጊዜ ከመድረሱ በፊት ስራዉ ተጠናቆ የጋራ ህገመንግስታዊ ሰነድ እንዲኖረን ቢደረግ፤

1.5. ህገመንግስቱን የማሻሻል ሂደት የፌደራል ስርዓት አወቃቀሩን ጭምር በማየት አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የክልል መንግስታት አከላለልን እስከመከለስ የሚዘልቅ መሆን ቢችል፤

1.6. የሚደረገዉ የፖሌቲካ ድርድር ዓላማ የጋራ አገራችንን ከተጋረጠባት አደጋ ለመታደግና ለቀጣይ ትዉልድ የተሻለች አገር ለማስተላለፍ  እስከሆነ ድረስ ስለአገራችን ያገባናል የሚሉ የፖሌቲካ ኃይሎች ሁሉ ከክብራቸዉና ከምኞታቸዉ በላይ ለአገሪቱና ለህዝቦቿ ክብር በመስጠት በሰለጠነ አኳኋን ለመቀራረብና ለመነጋገር ራሳቸዉን ማዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከዚህ አኳያ በገዥዉ ፓርቲዉ ኢህአዴግ በኩል ሽብርተኞች ናቸዉ ብሎ አቋም የያዘባቸዉ (ለምሳሌ፡ ግንቦት-7 እና የአርበኞች ግንባር፣ ኦነግ) ጭምር በተወካዮች ምቤት የወጣዉ አዋጅ እንደገና ታይቶም ቢሆን በድርድር ሂደቱ የመሳተፍ ዕድል ሊሰጣቸዉ ይገባል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በተቃዋሚዎች ጎራ ኢህአዴግ መጥፋት ነዉ ያለበት የሚል ከዴሞክራሲያዊ መርህ ያፈነገጠ አቋምና  ኢህአዴግን አሁን ባለዉ ህጋዊ ስያሜዉ እንኳን ለመጥራት ባለመፍቀድ ጭምር ”ወያኔ“ እያሉ ደርግ ወያኔን ለማጥፋት “ዓሳን ለማጥፋት ባህሩን ማድረቅ” በሚል የተሳሳተ አቅጣጫ ህወሀት ትግል የጀመረበትን የትግራይ ህዝብ ለማጥፋት ከወሰነዉ ዉሳኔ ብዙም የማይለይና አሁን የዓለምም ሆነ የአገራችን የህዝብ የአስተሳሰብ ከደረሰበት ደረጃ ጋር አብሮ የማይሄድ ፅንፍ ከረገጠ አቋማቸዉ ለህዝብና ለአገር ክብር ሲሉ ተስተካክለዉ ለኢህአዴግ ዕዉቅና በመስጠት ለመነጋገር ራሳቸዉን ዝግጁ ከማድረግ ጀምሮ የትግራይን ህዝብ ከአንድ የፖሌቲካ ፓርቲ (ህወሃት) መለየትና አቋማቸዉን ማስተካከል ይጠበቅባቸዋል፡፡

1.7. ህገመንግስቱና ከህገመንግስቱ የመነጩ ህጎች መሻሻላቸዉ አንድ ነገር ሆኖ ለመልካም አስተዳደር መስፈን አንዱና ዋናዉ ምሶሶ የሆነዉ የህግ በላይነትን የማክበር ጉዳይ ለዚህኛዉ ወይም ለዚያኛዉ አካል የሚተዉ ሳይሆን የሁሉም አካላት ግዴታ እንደሆነ ማመንና በቀጣይ የሚኖሩ አገራዊ ምርጫዎችም በህግና በህግ ብቻ የሚመሩ እንዲሁም አሸናፊዉ ከተሸናፊ የማይበልጥና ተሸናፊዉም የማያንስ እንደሆነ መቀበልና መከባበር ብሎም መቻቻል እንዲዳብር አዎንታዊ ሚና በመጫወት ሁሉም ለአገርና ለህዝብ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

2. **የኢኮኖሚ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን በሚመለከት**፡- ኢትዮጵያ የሁሉም ኢትዮጵያዊያን የጋራ ቤት እንደመሆኗ የህዝቦቿ ፍትሐዊ ተጠቃሚነት መረጋገጥ ይኖርበታል፡፡ በአንድ የቤተሰብ ተቋም ዉስጥ የሚገኙ የቤተሰብ አባላት ለቤተሰቡ መሻሻል አቅማቸዉ እስከፈቀደ ድረስ ድርሻ ማበርከታቸዉ የዉዴታ ግዴታቸዉ ነዉ፡፡ በዚህ ሂደት በሚገኘዉ መሻሻል ዉስጥ እያንዳንዱ የቤተሰብ አባል ሊያገኝ የሚገባዉ ድርሻ በማንም ሊነጠቅ አይገባም፡፡  በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት ከተነጠቀ ግን በዚያ ቤተሰብ ዉስጥ ሠላም እንዲኖር መጠበቅ ባዶ ምኞት ካልሆነ በስተቀር እዉን ሊሆን አይችልም፡፡ በተመሳሳይ መልኩ የአገርም ሁኔታ እንደዚሁ ስለሆነ ሁሉም ህዝብ እኩል የመሳተፍ ዕድል እንዲኖረዉ ምቹ ሁኔታ መፍጠርና በሂደቱም ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ አንፃር በአሁን ሰዓት እንደክፍተት የማያቸዉና ቢስተካከሉ የተሻለ ነዉ የምላቸዉ ጉዳዮች ቀጥሎ አቀርባለሁ፡፡

2.1. በኢህአዴግ በሚመሩ አራት ክልሎች (ደቡብ ብ/ብ/ህ/ክ፣ አማራ ክልል፣ ኦሮሚያ ክልል፣ ትግራይ) ዉስጥ የሚገኙና በ"ኢንዶዉመንት" ስም የተደራጁ የኢንቨስትመንትና የንግድ ተቋማት (በአማራ ክልል- ጥረት፣ በትግራይ ክልል-ኢፈርት፣ በኦሮሚያ ክልል ዲንሾ፣ በደቡብ ክልል ወንዶ) በአንድም ሆነ በሌላ ምክንያት የተቋቋሙበት ክልል ህዝብ ሀብት ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ ሀብት በመሆናቸዉ ወደ መንግስት የልማት ድርጅትነት መቀየር ቢችሉ፣

2.2. በመከላከያ ሚ/ር ስር የሚመሩ ትርፍን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች (ኢብኮ እና የመሳሰሉት) የሚመሩበት ስርዓት የመከላከያ ሚ/ር መረጃ ለአገር ደህንነት ሲባል በምስጢር መጠበቅ ያለበት እንደመሆኑና እነዚህ ትርፍን መሰረት ያደረጉ ድርጅቶች (በመንግስት በኩል ድርጂቶቹ ትርፍን መሰረት ያደረጉ አይደሉም እየተባለ የሚነገር ቢሆንም) ደግሞ በባህርያቸዉ ግልፅነት ከጎደላቸዉ ለሃሜት የተጋለጡና በግልፅ አሰራርና ቁጥጥር ካልተመሩ በስልጣን ለመባለግ ዕድል የሚሰጡ በመሆናቸዉ ለመከላከያ ከሚዉሉ የጦር መሳሪያዎችና ትጥቆች ዉጭ ያሉት በሲቭል አደረጃጀት እንደአንድ የመንግስት የልማት ድርጅት ሆነዉ የሚመሩበት የአሰራር ስርዓት ቢዘረጋ አገራዊ መተማመን በመፍጠር ለአገር አንድነት የራሳቸዉ አዎንታዊ ሚና እንደሚኖራቸዉ በማመን ተግባራዊ ቢደረግ፣

3. **የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በሚመለከት፡-** በመሰረቱ በአንድ አገር መንግስት የሚነደፉ የፖሊሲ ማዕቀፎች መሰረታቸዉ የአገሪቱ ህገመንግስትና ህገመንግስትን መሰረት አድርገዉ የሚወጡ ህጎች ናቸዉ፡፡ ከዚህ አንፃር አብዛኛዉ ህዝብና የፖሌቲካ ኃይሎች የተስማሙበት ህገመንግስታዊ ሰነድ እስከተፈጠረ ድረስ የትኛዉም ዓይነት ፖሊሲ (የግብርና ልማት፣ የማህበራዊ ልማት፣ ባህል ልማት፣ የዉጭ ግኙኝነት፣ ፋይናንስ፣ ወ.ዘ.ተ) የፖሊቲካ ፓርቲዎች መወዳደሪያ ማዕከል እንጂ መሆን ያለባቸዉ የግጭት መንስኤ መሆን የለባቸዉም፡፡ ስለሆነም የሚወጡ ፖሊሲዎች የተለያየ አመለካከት ባላቸዉ የፖሌቲካ ኃይሎችና የህብረተሰብ ክፍሎች አስተያየት እየተሰጠባቸዉና ጥልቅ ዉይይት እየተደረገባቸዉና አገሪቱ የደረሰችበትን ምጣኔ-ሀብታዊና ማህበራዊ ዕድገት የደረሰበትን ደረጃ ያማከለ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በየጊዜዉ እየዘመነ መሄድ በሚችልበት አግባብ እንዲቀረፅ ቢደረግ ለመስማማትም ሆነ ለመቻቻል የራሳቸዉ ሚና እንደሚኖራቸዉ በማመን ገቢራዊ ማድረግ የሚያስፈልግ ይመስለኛል፡፡

ስለሆነም ለአገርና ለህዝብ ስንል አገር ለመምራት ያለንን ምኞት ገታ አድርገን በቅድሚያ ለጋራ ቤታችን በጋራ ማሰብ ይጠበቅብናል፡፡ ከእዉነተኛ ልብ በመነጨ ስሜት ለህዝብ ራስን አሳልፎ ለመስጠት ቁራጥነት ከሌለና የመሪነት ተስጥኦ ሳይኖረን የግድ መሪ መሆን አለብን እያልን ከሆነ ደግሞ የራስ ምኞት ፍለጋ ካለን እርካሽ የግል ፍላጎት የሚመነጭ ግፊት ከመሆን አያልፍም፡፡ የመሪነት ተስጥኦ ሳይኖራቸዉ መሪ ለመሆን የሚታትሩ መሪ

የመሆን ፍላጎታቸዉ ለትክክለኛ ዓላማ ካላቸዉ የዉስጥ ፍላጎት ላይ ካልተመሰረተ አገርንም ሆነ ህዝቡን ይዞ ገደል እንደመግባት ነዉ፡፡ መሪነት ዋና ለመባል ባለዉ የግል ፍላጎት ላይ ብቻ ከተመሰረተ ፍፃሜዉ ስለማያምር በመሪነት ናፍቆት ብቻ የስልጣን ወንበር ለመቆናጠጥ ከመጣር ይልቅ አስቀድሞ ሊያስከትል የሚችለዉንም አገራዊ አደጋ ከወዲሁ መገንዘብ ጥቅሙ ጉልህ ነዉ፡፡ አሁን አገራችን ባለችበት ተጨባጭ ሁኔታ ከእኛዉ ፖሌቲከኞች አብዛኛዎቹ መሪ የመሆን ፍላጎት እንጂ የህዝብ መሪነት ተስጥኦ ያላቸዉ ስለመሆኑ ያጠራጥራል፡፡ ለዚህም ነዉ አንዲት ነፃነቷን ጠብቃ የቆየችዋን ታዳጊዋን ኢትዮጵያ የምትባል አገር ለመምራት ቁጥራቸዉ ከ60 በላይ የሆኑ የፖሌቲካ ፓርቲዎች ወደ ገደል አፋፍ እየፈጠነች ላለች አገራቸዉ መፍትሔ ከመስጠት ይልቅ ሁሉም መሪ ለመሆን ይታትራል፡፡ ቁጥራቸዉ የበዛ የብሄር፣ የሃይማኖት፣ የባህል፣ የቋንቋ፣ ወ.ዘ.ተ ስብጥር ባለባት አገር ሁሉም ፖሌቲከኛ መሪነት ከእኔ ወይም ከእኔ ወገን ዉጭ መሆን የለበትም ካለ ስንት ጠቅላይ ሚ/ር፣ ስንት ፕሬዚዳንት ወ.ዘ.ተ እንደሚያስፈልገን የሚቆጥረዉ ይቁጠረዉ፡፡ ከዚህ አንፃር ቢተገበሩ የአገራችን ሠላም መመለስና የኢኮኖሚ ዕድገቷንም ለማስቀጠል የራሳቸዉ የሆነ አዎንታዊ ድርሻ ይኖራቸዋል ብዬ የማግንባቸዉን ሃሳቦች ከላይ በአጭሩ ለማዉሳት ተሞክሯል፡፡ በአባባልም "ሰዉ ያለዉን ከወረወረ ንፉግ አይባልም" አይደል የሚባለዉ፡፡ የተነሱ ሃሳቦች በስፋት ሊተነተኑ የሚችሉ የዉይይት ሃሳቦች ናቸዉ ብዬ አምናለሁ፡፡ ታዲያ ሁላችንም ያለንን ሃሳብ በመሰንዘር አሁን አገራችን ላለችበት ችግር የመፍትሔ አካል መሆን የዉዴታ ግዴታችን እንደሆነ ከመቀበል ሌላ የተሻለ አማራጭ ያለን አይመስለኝም፡፡ በእኔ በኩል ለጊዜዉ ያለኝን በአጭሩ ለመሰንዘር ሞክራለሁኝና ሌሎቻችንም ላለንበት ተግዳሮት የመፍትሔ ሀሳብ እናዋጣ በማለት በማክበር እየጋበዝኩኝ የዛሬዉን በዚሁ አበቃሁ፡፡

ይበልጣል ታማኝ

ከሺሾ እንዴ ከተማ

03-07-18